# ወያኔ ከሱማሌ ጨርሶ ይወጣል ብሎ መገመት ወይም መሰል ድራማዎች መስራት ያቆማል ብሎ ማሰብ የማይታለም ነው ።

ከሄኖክ ጉርሙ

*ታኅሣሥ ፪፻፲፩ ዓ.ም*

ወያኔዎች ድሮም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማደናገር የደረሳችሁት ድርሰት እንጂ ኢትዮጵያን ሊወርም ሆነ ሊያሸብር ከናንተ የባሰ እንደማይመጣ ሕዝቡ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ወያኔ በዛው በሱማሌ የነበረው ኃይል በሁለት እግሩ መቆም ያልቻለና ለረጅም አመት ተወሳስቦባቸው የነበረባቸውን አገራዊ ችግር ለመቅረፍ ዜጎችዋ ባንድነት በተነሱበት ወቅት አገራቸው ያለባቸውን ጣጣ ቀርፈው ሳይጨርሱ ኢትዮጵያን ለማሸበር እንደተነሱ የወያኔው ሊ/መ በቴሌብዥን ጣቢያቸው በመግለፅ፤ በቤተ መንግስት ያፀደቁትን በምክር ቤታቸውም በድጋሚ በማፅደቅ፤ የተለመደ አስቂኝ ድራማቸውን አቅርበው ጦርነቱ የሕዝቡን ድጋፍ እንዳገኘ አስመሰሉ። በወቅቱ በሱማሌ እንኳን ለመቆየት የውጭ መንግስታትን እውቅናና ይሁንታ የተነፈገው ኃይል ኢትዮጵያን ለመውረርም ሆነ ለመዋጋት ያስባል ብሎ መገመት በጣም ይከብዳል ።

በወቅቱ ባገር ውስጥና በውጪ የደረሰበት አስደንጋጭ የፖለቲካ ኪሳራ፣ ውጪ ያሉ ኢትዮጵያን የሚያደርጉት የፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ እየጠነከረ መምጣትና የሰብአዊ መብት አስጠባቂ ድርጅቶች የሚያወጡት አስከፊ መግለጫዎች ለወያኔ መሪዎችና ለደጋፊዎቻቸው መራራ እየሆነ መምጣት፤ ይህና ይህን በመሰል እንቅስቃሴዎች ስጋት ውስጥ እንዲወድቁ የተገደዱት ወያኔዎች፤ ከዚህ አስደንጋጭ የፓለቲካ ክስረት ለመዳን እንደ አንድ የፖለቲካ ስልት አድርገው የተጠቀመት ሱማልያ ጣልቃ መግባት እና የአሜሪካን ፍላጐት በሟሟላት የወቅቱን የአሜሪካን አስተዳደር እይታ ለማደብዘዝ እንዲያስችል ከማድረጋቸውም ባለፈ ኢትዮጵያውያን ያደርጉት የነበረውን የፀረ ወያኔን እንቅስቃሴ ባለበት እንዳይቀጥል ለማስቻል በእጅጉ ተጠቅመውበታል።

ለወያኔ ይህ ድራማው በእጅጉ የተሳካለት ቢሆንም እናት በደሃ አቅሟ ያሳደገችውን የኢትዮጵያ ወታደር ለእሳት ዳረገ፤ በየ አውራ ጎዳናው እሬሳውን እንዲጎተት ፈቀደ፤ ወላጆችን ያለ ጧሪ ቀባሪ አስቀረ። አሁን ስለ እውነት ወያኔ እንደሚለው ስለ ኢትዮጵያ ዳር ድንበር መከበር ስለ ሕዝቧም ደህንነት በመቆርቆር ወደ ሱማሌ ገባ? ሕዝብን ለማደናገር እንጂ ለዘመናት ወላጆቻችን የወደቁለትን አገር አሳልፎ ለኤርትራ የሰጠ፣ ባህር በር አልባ ያደረገን፣ የባድመን መሬት በድጋሚ በሻቢያ እንድንነጠቅ ያበቃን፣ ሱዳን መሬታችንን የሸጠ፤ እህት ወንድሞች እናት አባቶቻችንን ባላቸው የፖለቲካ አመለካከት በጠራራ ፀኃይ በአደባባይ የነጠቀን ወያኔ፤ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን በስጋት በእስር ቤት ያለአግባብ አጉሮ እያሰቃየና በምን አይነት ሁንታ ላይ እንዳሉ እንኳዋን በማናውቅበት አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ከነ ነፍሱ ለመቅበር ጉድጓድ በመቆፈር ላይ የሚገኘው ወያኔ ስለ አገርና ስለወገን የቆመ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምና አንድነት ብሎም ዳር ድንበር ተቆርቋሪ በመምሰል ሱማሌ ጣልቃ እንደገባ መለፈፍ ምን ይባላል? የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊገለው ሊያሰቃየውና ብሎም ሊከፋፍለው ከወያኔ የባሰ አሸባሪ እንደማይመጣ ከተረዳ አመታት ተቆጥረዋል ።

ወያኔዎች ከመጀመሪያው ወደ ሱማሌ ፊታችሁን እንድታዞሩ ያስገደዳችሁ በወቅቱ

ተቀስቅሶባችሁ የነበረው የፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ ትግል ያየለና የተወሰኑ አገራትን እይታ በማግኘቱ ይህ ባለበት ቢቀጥል ኢትዮጵያውያንን ለበለጠ ትግል እንዲነሱ የሚያነሳሳ ከመሆኑም ባለፈ የወያኔን በስልጣን ላይ መቆየት አደጋ ውስጥ የሚጥልና ካድሬዎቹን በባሰ ወንጀል እንዲጠየቁ የሚያደርግ ሆኖ በመገኘቱ፤ ከዚህ የፖለቲካ ክስረት ለመዳንና በወንጀል የተጨማለቀን ማንነታችሁን አሸባሪነትን በመዋጋት ስም ልትደብቁና የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያደርገው ትግል ግቡን እንዳይመታ ለማድረግ፣ በዚህ ስም የሚመጣን የውጭ እርዳታ የካድሬዎቻችሁን ኪስ ማደለቢያ ለማድረግ፤ ይህ እና ይህን መሰል ግላዊና ድርጅታዊ ጥቅማችሁን ብቻ በማሰብ በሕዝባችን ይሁንታን ያላገኘ ጦርነት ገጠማችሁ። በውል የማይታወቁ ወገኖቻችንን አስጨረሳችሁ፤ የኢትዮጵያን ወታደር የሱማሌን ንፁሐን ሕዝብ ሕይወትና ንብረት እንዲጠፋ ምክንያት ሆናችሁ። የዚህ አምባገነን ስርአት መሪ ሰራዊታችን ሱማሌ እንዲገባ የተገደደበት ያሉት ምክንያትና አሁን የደረሱበት ውሳኔ እርስ በርሱ የሚጋጭ ከመሆኑም በላይ ከመጀመርያውም እዚያ የመግባታችሁ ሚስጥር ምን እንደሆነ በግልፅ የሚያሳይ ነው ።

በመሆኑም ሱማሌ የሚገኘው ኃይል ለኢትዮጵያ አስግቶ ሳይሆን የዚሁን የወያኔ ስርአት አራማጆችን እድሜ ለማርዘምና በዚሁ አሸባሪነትን በመዋጋት ዘመቻ ስም በወቅቱ ወያኔ ከደረሰበት የፓለቲካ ኪሳራ ለማገገም የተጠቀመው ስልትና ከውጪ መንግስታት ጫናና የተቀሰቀሰውን የፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ አቅጣጫ ለማስቀየር የፈጠራችሁት ድብቅ ስልታቹ ብቻ ነው ።

ወያኔ ስልጣንን ከጨበጠ ግዜ አንስቶ እኛ ኢትዮጵያውያን የትኛው በወያኔ ያገኘነው ሰላም እንዳይናጋ? የትኛው በወያኔ ተጠብቆ የቆየልን ድንበር እንዳይደፈር አስባችሁልን ነው? ወገኖቻችንን ለእሳት ለመዳረግ ሲታቅዱ እንኳን የውጪ መንግስትን የኢትዮጵያን ሕዝብ በቅጡ ያላማከራችሁ ወያኔዎች ዛሬ ከሱማሌ ልትወጡ መሆናችሁን ሱማሌ ብሎም ባካባቢው ያሉ አገሮች እኛ ከወጣን አለቀላቸው አይነት መግለጫ ለምን አስፈለገ? አቶ መለስ ምን በሚል ማሳሳቻ ሰራዊቱ ሱማሌ እንዲገባና ሕይወቱን እንዲያጣ አደረጉ? ሰሞኑንስ ምን በሚል መግልጫ አወጡ? ለኢትዮጵያ ስጋት የተባለው ኃይልስ አሁን በምን አይነት ሁኔታ ላይ ይገኛል? መልሱ ለብዙሓኑ ኢትዮጵያዊ ከተመለሰ ቆይቷል ።

ብቻ አሁን እኛ ኢትዮጵያውያን ከጦርነት ያተረፍነው ቢኖር እንደናንተ አይነት ከፋፋይ ጎጠኛ ኃይል እንዲዛዝን ማድረግና የደሃውን ቤተሰብ ማስጨረስ ብቻ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተቀዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዋች እንቅሴ እስካልተዳከመ፣ የውጪ መንግስታት ጫና እስካልቆመና በውጪና ባገር ውስጥ የሚደረገው የፀረ ወያኔ ዘመቻ እስካልጠፋ፣ ወያኔ ከሱማሌ ጨረሶ ይወጣል ብሎ መገመት ወይም መሰል ድራማዎች መስራት ያቆማል ብሎ ማሰብ የማይታለም ነው ።

ወያኔ በተለያየ ግዜ በፈፀማቸው የሰባአዊ መብት መጣስ ተግባሮች ከውጭ መንግስታትና ከሰብአዊ መብት አስጠባቂ ድርጅቶች የሚወጣው ጠንካራ ነቀፋ እንዲሁም ከውጪም ሆነ ከውስጥ ያጣው የፖለቲካ ኪሳራ የከፋ የነበረበትና የውጪ መንግስታትም ከወያኔ ጋር ሊኖራቸው የሚችለው ቀጣይነት በወቅቱ መልስ ያልተገለት በመሆኑ ወያኔ ከሌላው አገር ያለው ሳይሆን ከወደ አሜሪካ የሚመጣው ነቀፋና ጫና ሊከፋ እንደሚችል በማሰቡ የዚችን አገር ፉላጎት በሚሟላት ለጊዜውም ቢሆን እረፍት ያገኘና በወቅቱ የነበረውን የፀረ ወያኔ ዘመቻ ግብ እንዳይመታ የተጠቀመበት ከመሆኑም ባለፈ በወቅቱ ረቂቀ፣ ሕግ፣ 2003 በሚል የኢትዮጵያንን ሰላምንና ደህንነትን ለማዳበር፣ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ነፃነት

እንዲሰፍን ለማበረታታትና ለማመቻቸት በሚል በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ምክር ቤት ቀርቦ የነበረው እረቂቅ ህግ አጨራረሱ እንዳያምር የዚሁ የሱማሌ ጉዳይ ጠቅሟቸዋል በአሁኑ ሰአት።

የዚህ አምባገነን ስርአት ዋነኛ ደጋፊ የነበረው የቡሽ አስተዳደር ከአንድ ወር በኋላ ባለበት ሊቀጥል እንደማይችል የተገነዘበው ወያኔ የቀጣዩም የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የውጪ ፖሊሲ ጠንካራ መሆን፣ የተቃዋሚዎች ጠፍቶ አለመጥፋት ህዝቡ በጥቂቱም ቢሆን ልዩነቱን ትቶ ወደ አንድነት መምጣት በቡሽ ዘመን ግቡን እንዳይመታ የተደረገው ረቂቀ፡ ህግ፡ 2003 የቀጣዩን ፕሪዝዳንት ድጋፍ እንደሚጠብቅ የተረዳው ወያኔ አሁንም በድጋሚ በኢትዮጵያ ውስጥ እድሜዬን ያረዝማሉ ብሎ ያሰባቸውን ሁሉ እያደረገ ነው።

በቅርቡም የሱማሌን ጉዳይ ይዞ ብቅ ያለ ከመሆኑም በላይ ሱማሌ ብሎም ባካባቢው ያሉ አገራት ሰላም አስጠባቂ እሱና እሱ ብቻ እንደሆነ ለማስመሰል የውጪን አገሮች ቀልብ ለመሳብና ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ያደረሰውን ሰብዓዊ ጥፋት ተሸፋፍኖ እንዲቀጥል እንዲያስችለውና በቀጣይ ሊፈፅማቸው ያሰባቸውን ካድሬአዊ እቅዶቹን ለማሳካት በዚቹ በሱማሌ ጉዳይ ለመጠቀም እንዲያስችለው የውጪ መንግስታት በተልይ አዲሱ የአሜሪካ መንግስት በቀጣይ የወያኔን አስተዳደር በተመለከተ የሚወስዱት እርምጃም ሆነ የሚያወጡት መግለጫ ከቡሽ ዘመን የከፋ እንዳይሆን ለማድረግ የታቀደና፤ ኢትዮጵያን ለመመልከት ቢያስቡ እንኳን ሱማሌን ማየት እንዲኖርባቸው ለማድረግ የተሞከረ እንጂ፤ መች ከሱማሌ ጠቅልሎ ሊወጣ ሆነና ወያኔ ይህ እኩይ ተግባሩ ሳይሳካ ከሱማልያ ተገፍቶ እንዲወጣ ቢገደድ እንኳን ፊቱን ወደ ኤርትራ በማዞር መሰል ድራማ መስራቱ አይቀሬ ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለፈውና አሁን ከሚሰራው የወያኔ ድራማ በመማር ለቀጣዩ ትግል ባንድነት እንነሳ። በውስጥም በውጭም ያላችሁ ተቃዋሚዎች በመጀመርያ ያሉባችሁን የቋንቋና የብሔር ፖለቲካ ችግራችሁን በማጥፋት፤ ውስጣዊ የስልጣን ጥማታችሁን በማሶገድ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባንድነት የሚያሳትፍ አገራዊ አጀንዳ በመንደፍ ሕዝቡን የስልጣን ባለቤት እንዲሆን አስችሉ።

ማናቸውንም አይነት የራስን የፖለቲካ ድርጅትንም ሆነ ብሔርን የተሻለ እንደሆነ ለማድረግ የሚደረግ የተናጠል የድል ዜናም ሆነ ትግል ሕዝቡን ለባሰ ስቃይና ሞት ከመዳረግ ያለፈ የትም እንዳላደረሰ ባለፉት አመታት በተግባር ያሳያችሁን በመሆናችሁ ልዩነታችሁን ወደጎን በመተው ኢትዮጵያን ሁሉ ባንድነት ከጎናችሁ እንዲቆሙ አስችሉ ።

በትክክል ስለ ሕዝቡ የቆማችሁ ከሆነና በቀጣዩ አመት የሕዝቡን ስቃይና ሞት ማየት የማትሹ ከሆነ የየፓርቲያችሁ አናት ላይ ለመቀመጥ የምታደርጉትን መሰባበርና ሽኩቻችሁን በቅድሚያ በማቆም ወያኔን በአንድነት የሚታገል ሕዝብ በመፍጠር ታሪካዊ ድል አስመዝግቡ። ይህ ካልሆነ ግን አንዱ ፓርቲ በምርጫ ለማሸነፍ ቢችል እንኳን አርቆ ባለማሰብ ሌላው የተቀዋሚ ፓርቲ እንቅፋት የሚሆንበት እንዲሁም፤ ኦሮሞው በድል ወደ ከተማ ሲቀርብ አማራ ለወያኔ ጥይት የሚያቀብልበት፤ አማራው ወደ ድል ሲጠጋ ሌላው ከወያኔ ጋር አብሮ የሚያብርበት ግዜ እንደሚመጣ አልጠራጠርም።

Contact
henokgurmu@yahoo.com